በአዉሮፓ አቀፍ የአንድነት የድጋፍ ድርጅቶች ጊዜያዊ አስተባባሪ ግብረ ኃይል የተሰጠ የአቋም መግለጫ !!!

# <u>የነጻነትን ራዕይ በአፈና በተጋረደ የምርጫ ዉጤት ማጥፋት አይቻልም</u>

በአገራችን ረጅም ታሪክ የስልጣን ሽግግር ከጠብ መንጃ አፈሙዝ የሚገኝ የጉልበት ተግባር እንጂ በህዝብ ይሁንታ የሚመጣ የምርጫ ዉጤት አለመሆኑ በተደጋጋሚ በተግባር ታይቷል:: ዛሬ በ21ኛዉ ክፍለዘመን ዓለም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዳብሮ የሰዉን ልጅ ፍላጎት ከሞላ ጎደል የተሟላ እንዲሆን እያደረገ ባለበት ወቅት እንኳን ህዝባችን ፍትህና ነጻነት እንደሰማይ ርቆት በመሰቃየት ላይ ይገኛል::

ለበጎ ነገር አለመታደሉ ከህዝባችን ፍላጎት እጦት ወይንም ችሎታ ማነስ የመጣ አይደለም:: በህዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ የግል የስልጣን ጥም የተጠናወታቸዉና ቅንነት የጎደላቸዉ ስግብግብ መሪዎች ስለሚያጋጥሙን ብቻ ነዉ:: ከእንዲህ አይነቱ አዙሪት ለመላቀቅ የሚቻለዉ በግለሰቦችና  ጥቂት ቡድኖች ተጋድሎ ወይንም መልካም ፈቃድ ሳይሆን የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነዉን ሰፊዉን የኢትዮጵያ ህዝብ በማደራጀትና በማሳተፍ ነዉ::

እንዲህ አይነቱን ሁሉ አቀፍ እንቅስቃሴ መርቶ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ባይተዋር በሆነና በጉልበት ታፍኖ በተያዘ ህብረተሰብ ዉስጥ ለመተግበር የሚጠይቀዉ መስዋዕትነት ቀላል አይደለም:: በመሆኑም ነዉ የግንቦት ሰባቱን 2005 ምርጫ ተከትሎና ከዚያም በኋላ እስካሁን ድረስ እየተከፈለ ያለዉ መስዋእትነት ከፍተኛ የሆነዉ::

የወያኔ መንግሥት የ2005 ምርጫ ቅሌት እንዳይደገም አምስት ዓመት ሙሉ የአፈና መረቡን ሲዘረጋ ሰንብቶ ብቻዉን ሩጦ ብቻዉን አሸነፍኩ ለማለት አቅዶት ነበር ነገር ግን በአንድ ወቅት ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ሜዳዉን በምንም አይነት ለወያኔ አንለቅም ባለችዉ መሰረት ፓርቲዋ የ2010 ምርጫን ተሳትፎ የእህአዴግን የምርጫ ድራማ ለአለም ህብረተሰብ አጋልጧል:: በመሆኑም እኛ በአዉሮፓ አቀፍ ተደራጅተን አንድነት ፓርቲን የምንደግፍ ኢትዮጵያዉያን የድርጅቱን እንቅስቃሴና የምርጫዉን ህደት አስመልክቶ ባካሄደነዉ የጋራ ግምገማ የሚከተለዉን አቋም ወስደናል:-

1. የወያኔ መንግሥት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መሪ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ከማሰር አንስቶ የተለያዩ ደባዎችን በመፈጸም ፓረቲዉን ለማፍረስ ያደረገዉን ጥረት በመቋቋምና ይበልጥ በመጠናከር አንድነት ህብረት ፈጥሮ ከመድረክ አባል ድርጅቶች ጋር ያደረገዉን ሁሉ አቀፍ ትግል እናደንቃለን::

2. አንድነት ከዉስጥና ከዉጭ አጋጥሞት የነበረዉን ችግር ተቋቁሞ በአጭር ጊዜ ዝግጅት ብዛት ያላቸዉን ተሳታፊዎች ለምርጫዉ በማቅረብ ትልቅ ተፎካካሪ ፓርቲ

ለመሆን መብቃቱ የአመራሩን ጥንካሬና ቁርጠኝነት የሚያመለክት በመሆኑ አበረታች ነዉ::

3. በዚህ አጋጣሚ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ሲታገሉ በወያኔ ቅጥረኞች ለተገደሉ፣ የአካል ጉዳትና ሌሎችም ተመሳሳይ በደል ለደረሰባቸዉ የፓርቲዉ አባላትና ደጋፊዎች ያለንን አክብሮት እንገልጻለን::

4. የወያኔ መንግሥት ምርጫዉን አጭበርብሮ፣ ህዝባችንን በጠብ መንጃ አፍኖና አስፈራርቶ ለመግዛት እያደረገ ያለዉን ህገ ወጥ ተግባር አጥብቀን እንቃወማለን::

5. አንድነትና ሌሎችም የመድረክ አባል ድርጅቶች ለምርጫዉ ባካሄዱት ዝግጅት፣ በምርጫዉ ወቀትና አሁን ከምርጫዉ በኋላ ከወያኔ መንግሥት ለሚሰነዘሩበት ፈርጀ ብዙ ጫናዎችና ድለላዎች ሳይበገር እየወሰደ ያለዉን አቋመ ጽኑ ዉሳኔ እናደንቃለ::

6. በኮሚነስታዊ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የእዝ ሰንሰለት በማስፈራራት፣ በማጭበርበርና በስርቆት ከህዝብ ፍላጎት ዉጭ አሸነፍኩ ብሎ ያወጀዉን 99.6% የምርጫ ዉጤት እናወግዛለን::

7. ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በጠየቁት መሰረት የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ተፈተዉ ፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፍቶ፣ ነጻ የሚዲያ አዉታሮች ተፈቅደዉ፣ ነጻና ገለልተኛ ታዛቢዎች በተገኙበት ምርጫዉ እንዲደገም እንጠይቃለን::

8. የድጋፍ ድርጅቶቻችን ይህንን አስከፊ ስርአት ከህዝባችን ጫንቃ ለማዉረድ በምታካሂዱት ትግል አስፈላጊዉን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን ::

04.06.2010

1Crowndale Road London NW1 1TU Mob: 07946644831 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk